# ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ታክስ ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 145/2011

መጋቢት 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 145/2011

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ድርጅቶችና መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ ሰፊ የአገር ውስጥ ግብይት ላላቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች ኃላፊነቱን በመስጠት የታክስ ባለስልጣኑን የመረጃ ምንጭ ማስፋት በማስፈለጉ፣

በተመረጡ የንግድ ዘርፎች የተሰማሩ ግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት በመስጠት የንግድ ውድድሩን ፍትሀዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈለውን የንግድ ትርፍ ግብር በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆነውን አሰራር መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 92(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 145/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ፡-

1/ **"ግብር"** ማለት በዚህ መመሪያ የተገለፁት ግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በመቀነስ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የሚያደርጉት የንግድ ትርፍ ግብር ነው።

2/ **"የምዝገባ ምስክር ወረቀት"** ማለት ግብር ቀንሶ እንዲያስቀር ኃላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ግብር ከፋይን ግብሩን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ እንዲያስቀር ውክልና የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው።

3/ **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር፣የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ገቢ ሰብሳቢ አካላት፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም ይጨምራል።

4/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን የሚኒስቴሩን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይጨምራል።

5/ **"አዋጅ"** ማለት የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ማለት ነው።

6/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ እና በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

7/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴትም ተፈጻሚ ይሆናል።

3. <u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች</u>

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በአዋጁ አንቀፅ 92 ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 2% ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ በዚህ መመሪያ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል።

2/ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው የደረጃ "ሀ" ግለሰብ ግብር ከፋዮች ባለፉት ሶስት

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

ተከታታይ ዓመታት በአማካይ 10 ሚሊዮንና ከዚያ በላይ ጠቅላላ ገቢ ያስመዘገቡ ግለሰብ ግብር ከፋዮች ናቸው።

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ቀጥሎ በተመለከቱት የንግድ ስራ ዘርፎች የተሰማሩ የደረጃ "ሀ" ግለሰብ ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢያቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡-

ሀ) ማንኛውም ባለ ኮከብ ሆቴል ወይም ማንኛውም ሪዞርት፤

ለ) ከ1 እስከ 4 ደረጃ ያላቸው ሥራ ተቋራጮች፣

ሐ) ማንኛውም የሪል ስቴት አልሚ፤

መ) የምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች፤

ሠ) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግገር የሚፈፅም ማንኛውም ግለሰብ ግብር ከፋይ በምርት ገበያው በኩል ላደረገው ግብይት ብቻ፣

ረ) ሆስፒታሎች እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መስፈርት መሰረት ከፍተኛ እና ከዚያ በላይ ደረጃ ያላቸው ክሊኒኮች፣

ሰ) ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች ፣

ሸ) ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት በመረከብ የሚያከፋፍል ማንኛውም ግለሰብ ግብር ከፋይ፣

4. <u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1/ የታክስ ባለስልጣኑ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ግለሰብ ግብር ከፋዮች በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት ከተከፋይ ሂሣቦች ላይ ግብር ቀንሰው ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለባቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታቸውን መወጣት የሚጀምሩት በታክስ ባለስልጣኑ ተመዝግበው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከተሰጣቸው ቀን ጀምሮ ይሆናል።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

3/ በዚህ መመሪያ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር በመቀነስ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተጣለባቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚወስዱት ግብር ከሚከፍሉበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር በላይ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ግለሰብ ግብር ከፋይ፡

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን መስፈርት የንግድ ስራ በሚያከናውንባቸው ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች በተናጠል አሟልቶ ሲገኝ ግብር ከፋዩ ዋና የንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት በወሰደበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ተመዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በመውሰድ ግብሩን ሰብስቦ ይከፍላል፡፡

(ለ) በተለያዩ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ከሚያከናውናቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚያገኘው የተናጠል ገቢ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን አማካይ የገቢ መጠን የማያሟላ ቢሆንም በሁሉም ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሚያገኘው ጠቅላላ አማካኝ ገቢ በመመሪያው አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን መመዘኛ የሚያሟላ ከሆነ ዋና የንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት በወሰደበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ተመዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በመውሰድ ግብሩን ሰብስቦ ይከፍላል፡፡

5/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2) የሚሸፈን ግለሰብ ግብር ከፋይ በተለያዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የንግድ ስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) እና (ለ) የተመለከተው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ መቀነስ ያለበት የንግድ ትርፍ ግብር እና አፈጻፀሙ

በዚህ መመሪያ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሶ እንዲያስቀር ኃላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ግብር ከፋይ ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በሚያከናውነው ግብይት ላይ ተቀናሽ መደረግ ያለበትን ግብር ቀንሶ በማስቀረት ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

## 6. ስለደረሰኝ

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች ከታክስ ባለስልጣኑ ፈቃድ በመውሰድ ደረሰኝ አሳትመው መጠቀም አለባቸው፡፡

## 7. የገቢ ሂሣብ አመዘጋገብ እና ትልልፍ

ግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ገቢ ያደረገውን ግብር ግብሩ ገቢ የተደረገለት የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን የየራሳቸውን ድርሻ በማስቀረት የሌሎችን ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም የፌደራል ድርሻ በመለየት አግባብነት ባለው የሂሳብ ኮድ በመመዝገብ ከዝርዝር መረጃው ጋር በወቅቱ ያስተላልፋል፡፡

## 8. ግብሩን ቀንሶ የሚያስቀር ግለሰብ ግብር ከፋይ ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ለሚመለከተው የታክስ ባለስልጣን ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ግለሰብ ግብር ከፋይ በገቢ ግብር አዋጁ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሰው እንዲያስገቡ ኃላፊነት ለተጣለባቸው ድርጅቶችና መስሪያ ቤቶች የተደነገጉ ግዴታዎች ያሉበት ሲሆን በታክስ አስተዳደር አዋጁም በእነዚሁ ድርጅቶች እና መስሪያ ቤቶች ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች እና የወንጀል ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ............. ቀን 2011 ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**
**የገቢዎች ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**